# የእርስዎ ክትባት፡ ምን መጠበቅ እንዳለብዎት

ሬኒየር ቢች ጣቢያ

በደቡብ ምስራቅ ሲያትል የአረጋውያን ማዕከል በሚገኘው በሲያትል ከተማ ሬኒየር ቢች የክትባት ክሊኒክ ውስጥ ለክትባት ቀጠሮ ስላስያዙ እናመሰግናለን።

ጉብኝትዎ በተቻለ መጠን እንከን የለሽ እና ደህንነቱ የተጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ፣ እባክዎ ምን እንደሚያመጡ፣ የት እንደሚሄዱ እና ምን እንደሚጠብቁ ዝርዝሮችን ለማግኘት ከጉብኝትዎ በፊት ይህን መረጃ ይገምግሙ። ማንኛውም ዓይነት ጥያቄ ካለዎት ወይም የአካል ጉዳተኛ ማረፊያን ለመጠየቅ ከፈለጉ እባክዎን ወደ የሲያትል ከተማ የደንበኞች አገልግሎት ቢሮ ከሰኞ እስከ ዓርብ ከጥዋቱ 8 እስከ ምሽቱ 5 በ (206) 684-2489 ይደውሉ። የውስጥ ቋንቋ አገልግሎቶች በስልክ እና በክትባቱ ጣቢያም ይገኛሉ።

## ከቀጠሮዎ በፊት

ለራስዎ እና ለሌሎች ጤንነት እና ደህንነት ሲባል፣ እባክዎትን የሚከተሉት ምልክቶች ካሉብዎት በቀጠሮዎ ላይ አይገኙ:

- የኮቪድ-19 ሕመም የሚመስሉ ማንኛቸውም ምልክቶች እንደ ትኩሳት፣ የጉሮሮ ሕመም ወይም ሳል የመሳሰሉ ካሉብዎት፤ ወይም
- ባለፉት 14 ቀናት ውስጥ ከኮቪድ-19 ምርመራ አወንታዊ የሆነ ግለሰብ ጋር የቅርብ ግንኙነት ኖሮት ከሆነ።

## ወደ ቀጠሮዎ ምን ይዘው እንደሚመጡ

- ፎቶ ያለው መታወቂያ (ካለዎት፤ የግድ አይደለም)። ፎቶ ያለው መታወቂያ ከሌለዎት፣ አሁንም በነጻ ክትባት መውሰድ ይችላሉ።
- ጭምብል ወይም የፊት ሽፋን
- ክትባቱን በላይኛው ክንድዎ አካባቢ በቀላሉ ለመስጠት እንዲቻል፣ ጉርድ እጅጌ፡ ወይም እጅጌው ወደላይ በቀላሉ መሰብሰብ የሚችል ልብስ ይልበሱ።
- ሁለተኛውን ወይም ለማጠናከሪያ ተጨማሪ የከትባት መጠን እየተቀበሉ ከሆነ፣ የክትባት ማረጋገጫ። የክትባት ማረጋገጫ ከሌለዎት፣ አሁንም ቢሆን ሁለተኛውን ወይም ተጨማሪ የማጠናከሪያውን የክትባት መጠን ማግኘት ይችላሉ።

## ይዘው መምጣት የሌለብዎት

- የቤት እንስሳት (የአገልግሎት እንስሳ ካልሆነ በስተቀር)
- ጓደኞች እና ቤተሰብ ወደ ክትባት ክሊኒክ። የልጅ ተንከባካቢ ከሌለዎት ወይም እርዳታ ከፈለጉ፣ ልጆችን ወይም እርዳታ የሚሰጥ ሰው ማምጣት ይችላሉ። ክትባቶች ቀጠሮ ላላቸው ግለሰቦች ብቻ ይሰጣሉ። ጓደኞች እና ቤተሰብ ከምልከታ ቦታ ውጭ ሊጠብቁዎት ይችላሉ።

## በየትኛው ሰዓት ላይ መድረስ እንዳለብዎት

እባክዎን በተቻለ መጠን በቀጠሮ ጊዜዎ ይድረሱ። ክትባቱ አያልቅብንም፣ እና መከተብዎን ለማረጋገጥ ቀደም ብለው መድረስ አያስፈልግዎትም። ቀጠሮ ካለህ ክትባቱን ትወስዳለህ።

## እዚያ እንዴት እንደሚደርሱ

ደቡብ ምስራቅ ሲያትል ሲኒየር ማእከል በ4655 S. Holly St. Seattle, WA 98118 ይገኛል። በመንገድ ላይ የመኪና ማቆሚያ አለ። ተጨማሪ የመኪና ማቆሚያ በቀጥታ ከቺፕ ቺካዴ ትሪፍት ስቶር ጀርባ እና በማዕከሉ ስር ባለው በቀጥታ ወደ ሊፍት መዳረሻ ባለዉ የመኪና ማቆሚያ ጋራዥ ውስጥ አለ።

ደቡብ ምስራቅ ሲያትል ሲኒየር ማእከል በኪንግ ካውንቲ ሜትሮ መስመሮች 7፣ 50 እና 106 በቀላሉ ማግኘት ይቻላል፡

- መስመር 7፡ ከሁለቱም አቅጣጫ S Holly St ላይ ከአውቶቡስ ይውረዱ። ወደ ደቡብ ምስራቅ ሲያትል ሲኒየር ሴንተር መግቢያ በ S Holly St ከ Rainier Ave S በስተ ምዕራብ ይገኛል።
- መስመር 50፡ ከሁለቱም አቅጣጫ S Holly St ላይ ከአውቶቡስ ይውረዱ። Rainier Ave S እስከትደርሱ ድረስ በS Holly St ላይ ወደ ምዕራብ ይራመዱ። ወደ ደቡብ ምስራቅ ሲያትል ሲኒየር ሴንተር መግቢያ በRainier Ave S ማዶ በS Holly St ይገኛል።
- መስመር 106፡ ከሁለቱም አቅጣጫ ከአውቶቡሱ በS Holly St. ይራመዱ ወደ ምስራቅ በኤስ ሆሊ ሴንት ይራመዱ። የደቡብ ምስራቅ ሲያትል ሲኒየር ማእከል ሬኒየር አቬ ኤስ ከመድረስዎ በፊት በቀኝዎ ይሆናል።




ለተጨማሪ የመጓጓዣ መረጃ እና አቅጣጫዎች፣ እባክዎን tripplanner.kingcounty.gov ን ይጎብኙ። ከ እና ወደ ማንኛውም የክትባት ጣቢያ ነፃ የመጓጓዣ መሳፈሪያዎች በ ሊፍት (Lyft) እና ሆፕሊንክ ሞቢሊቲ (Hopelink Mobility) በ(ስልክ: 425-943-6706) ይገኛል።

## እዚያ ሲደረሱ ምን መጠበቅ እንዳለብዎት

### 1ኛ ደረጃ: መምጣትዎን ማስረገጥ (Check-In)

በግልጽ ምልክት የተደረገበት የመግቢያ እና የክትባት መስመር ያስገባሉ። በቀጠሮዎ ጊዜ ሁሉ ጭምብልዎን መልበስ እና ማህበራዊ ርቀትዎን መጠበቅ ይጠበቅብዎታል። የሲያትል የእሳት አደጋ መከላከያ ክፍል (SFD) ቡድን አባላት የቀጠሮ ማረጋገጫ ኮድዎን በመጠየቅ ቀጠሮዎን ለማረጋገጥ ይረዱዎታል። የማረጋገጫ ኮድዎ ከሌለዎት በጎ ፈቃደኞች ስምዎን እና የልደት ቀንዎን ይጠይቃሉ። የሰጡት ስም በዚያ ጊዜ ቀጠሮ ከተያዘለት ስም ጋር መመሳሰል አለበት። ፎቶ ያለው መታወቂያ ካለዎት፣ ለማሳየት ዝግጁ መሆንዎን ያረጋግጡ፣ ነገር ግን መታወቂያ የግድ አያስፈልግም። የSFD ቡድን አባል የእርስዎን የግል እና የመገኛ መረጃ ያረጋግጣል። እንዲሁም ጥቂት የግዴታ የጤና ማጣሪያ ጥያቄዎችን ይጠይቅዎታል። ይህ ክፍል ለሦስት ደቂቃዎች ያህል ይቆያል።

### 2ኛ ደረጃ: ክትባትዎን መውሰድ

ክትባታችሁ የሚተገበረው በሲያትል የእሳት አደጋ መከላከያ ዲፓርትመንት የእሳት አደጋ ተከላካዮች/ፓራሜዲኮች በአንዱ ነው። እባክዎን ክትባቱን እንዲወስዱበት የመረጡ ክንድዎን እጅጌዎን ወደላይ ይሰብስቡ። የቁስል መሸፈኛ ይደረግልዎታል እና እየወሰዱ ስላለው ክትባት መረጃ ይሰጥዎታል። ይህ ክፍል አንድ ደቂቃ አካባቢ ይቆያል።

### ደረጃ 3: በምልከታ አካባቢ ዉስጥ ዘና ይበሉ

በእኛ ምልከታ ቦታ ላይ ይቀመጡ እና ሰዓት ቆጣሪ ለ 15 ደቂቃዎች ያዘጋጁ። ከዚህ በፊት በክትባት ምክንያት የመድኀኒት እንደ ደረቅ ምች ያለ ምላሽ አጋጥሞዎት ከሆነ፣ እባክዎን ለ30 ደቂቃዎች በምልከታው አካባቢ ይቆዩ። የሲያትል የእሳት አደጋ መከላከያ መምሪያ የመጀመሪያ ምላሽ ሰጭዎች ጥቂት ሜትሮች ብቻ ይርቃሉ እና ለሚፈልጓቸው ማናቸውም ፍላጎቶች መርዳት ወይም ማንኛውንም ጥያቄዎች መመለስ ይችላሉ። ከ15 ደቂቃዎች በኋላ ወደ ቤት መሄድ ይችላሉ! አብዛኛውን ጊዜ፣ አጠቃላይ ሂደቱ ለ 30 ደቂቃዎች ያህል ይቆያል። የክትባት ማጠናከርያውን እየተቀበሉ ከሆነ፣ በክትባት ምልከታው አካባቢ ውስጥ መቆየት አያስፈልግዎትም እና ክትባቱን ተከትሎ ወዲያውኑ ወደ ቤት መሄድ ይችላሉ።

### ደረጃ 4: ተከትበዋል!

የ Moderna ወይም Pfizer ክትባቶችን እየተቀበሉ ከሆነ ሁለተኛ መጠንዎን እንዳይረሱ የቀን መቁጠሪያ ቀጠሮ ይያዙ። በመከተብዎ እንኳን ደስ አለዎት!